አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)

LION INSURANCE COMPANY (S.C.)

# የባለአክሲዮኖች 18ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ 393(2) እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 14 መሠረት የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.) የባለአክስዮኖች 18ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ቅዳሜ ታህሳስ 18 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንዲገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል።

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች፣

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥርያ ቤት አድራሻ:- አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 04፣ የቤት ቁጥር 049 (አንበሳ ኢንሹራንስ ሕንፃ)፣ ፖስታ ሣ.ቁጥር፡ 26281/1000፣ ኢ-ሜል፡ lioninsurance@ethionet.et፣ ድህረ-ገጽ፡ http://www.anbessainsurance.com

1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር:- RK/AA/3/0002724/2006

1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈቀደ ዋና ገንዘብ (ካፒታል):- ብር 1.2 ቢሊዮን ፤

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ እና የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል):- ብር 562.43 ሚሊዮን፤

1.5. የአክሲዮን ማህበሩ አይነት:- በጠቅላላ መድን እና በረጅም ጊዜ /ህይወት/ መድን ሥራዎች ላይ የተሰማራ አ.ማ።

## 2. የአስራ-ስምንተኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፣

2.1. ከአስራ-ሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፤

2.2. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርትን ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.3. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የሒሳብ ዘመን የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርትን ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.4. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የሒሳብ ዘመን የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

2.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2025/26 ወርሃዊ አበል እና እ.ኤ.አ. የ2024/25 ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ክፍያን መወሰን፤

2.6. የውጭ ኦዲተሮች የክፍያ መጠን ማሻሻያ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ማካሄድ።

## 3. ማሳሰቢያ፣

3.1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በአንበሳ ኢንሹራንሽ ሕንፃ ዋና መ/ቤት በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

3.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

**የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)**
**በዳይሬክተሮች ቦርድ ትዕዛዝ!**

ዋናው መ/ቤት: ኃይሌ ገ/ሥላሴ ጎዳና፣ አንበሳ ኢንሹራስ ህንፃ
011-618 80 00/618 70 00 ፋክስ፡ 011 663 2940/ 635 20 40
26281/1000
Info@anbessaInsurance.com
www.anbessaInsurance.com

በአገልግሎቱ የሚረኩበት፣ በጥንካሬው የሚመኩበት!!

For Rellable Service and Dependable Capacity!!